# የኢትዮ-ኤርትራ የካሣ ኮሚሽን የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮ-ኤርትራ የካሣ ኮሚሽን በአልጀርስ የሰላም ስምምነት መሠረት ከተቋቋመ አንስቶ ካስተላለፋቸው ውሳኔዎች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀሰው የኤርትራ መንግሥት የተባበሩት መንግሥታት ቻርተርን አንቀጽ 2(4) በመጣስ በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ ወረራ መፈፀሙ ነው።

ይህ የካሣ ኮሚሽን ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. ባስተላለፈው ውሳኔ ተልዕኮውን ማጠናቀቁ እና የመጨረሻውን የካሣ መጠን አከፋፈል ውሳኔ አስተላልፏል። ውሳኔው በርካታ የቴክኒክ ነክ የሆኑ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ቢሆንም ዋና ዋና ክፍሎቹን ለመጥቀስ ያህል ለኢትዮጵያ የአሜሪካ ዶላር 174,036,520 በሌላ በኩል ደግሞ ለኤርትራ በመንግሥት ስር ለቀረቡ የአሜሪካን ዶላር 161,455,000 እና በተወሰኑ ግለሰቦች ስም ለቀረቡ አቤቱታዎች የአሜሪካን ዶላር 2,065,865 የጉዳት ካሣ ገንዘብ ክፍያ ወስኗል።

ለኢትዮጵያ የተሰጠው የካሣ ክፍያ ገንዘብ መጠን መሠረት የሚደረገው ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ መፈፀሟን በማረጋገጥ ኮሚሽኑ ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ነው። በዚህ መሠረት ከተላለፉት የካሣ መጠን ውሳኔዎች መካከል በኢትዮጵያውያን ሰላማዊ ሰዎች ላይ የደረሱ የሞት፣ የአካል ጉዳት፣ የሕዝብ፣ የግል፣ የንግድ እና የሃይማኖት ድርጅቶችን ንብረት መዝረፍ፣ ማውደም፣ መፈናቀል፣ በጦር ምርኮኞች ላይ ጉዳት ማድረስ እንዲሁም በተቀበሩ ፈንጂዎች ሞትና የአካል ጉዳት ማድረስ የሚሉ ይገኙባቸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ኮሚሽኑ ኤርትራ የቬየና የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶች ኮንቬንሽንን በመጣስ በአስመራ የነበሩት የኢትዮጵያን ጉዳይ ፈፃሚ በማሰርና በማገቷ፣ እንዲሁም የዲፕሎማቲክ መልዕክቶችን ልውውጥ በግልጽ በመጣስ እና የሚሲዮኑን ሥራ በማወኳ ለካሣ ክፍያ ኃላፊነት ተጠያቂ አድርጓታል። በዚህ ረገድ ለኤርትራም የዲፕሎማቲክ ሚሲዮንን መብት ተጥሷል በማለት የተሰጠ ካሣ የተወሰነላት ቢሆንም ኤርትራ የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈፃሚን በማሰርና በማገት ከፈፀመችው ሕገ-ወጥ ተግባር ጋር የሚወዳደር አይደለም። ለኤርትራ የተወሰኑት ሌሎች ጉዳዮች በአብላጫው የሚመለከቱት ኢትዮጵያ የኤርትራን ወረራ ለመቀልበስ በወሰደችው የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ደርሰዋል የተባሉ የንብረት ጉዳቶችን ይመለከታሉ።

ለሁለቱ አገሮች የተወሰኑት የገንዘብ ካሣ መጠኖች ሲሰሉ ለኢትዮጵያ የተወሰነው የካሣ መጠን ገንዘብ ከ10,000,000 የአሜሪካን ዶላር በልጦ ይገኛል። ይህ መጠን ኮሚሽኑ ራሱ ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ ፈፅማለች በማለት ካሳለፈው የወራሪነት ወንጀል ክብደት አንፃር እጅግ አነስተኛ መሆኑ እሙን ነው። ምንም እንኳን ይህ መጠን ኤርትራ ከፈፀመቻቸው ጥፋቶች ጋር የተመጣጠነ ባይሆንም ኤርትራ ዓለምአቀፍ ሕግን በመጣስ የፈፀመቻቸውን በርካታ ጥፋቶች በድጋሚ ገሀድ የሚያወጣ ነው። በተለይም ይህ ውሳኔ የተወሰነው ኤርትራ በአፍሪካ ቀንድ በምትፈፅማቸው የፀረ-ሰላም እና አካባቢውን የማወክ ድርጊቶች ማዕቀብ እንዲጣልባት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት እየመከረ ባለበት ወቅት በመሆኑ ይህ ውሳኔ መተላለፉ የኤርትራን አጥፊነት ገሀድ የሚያደርግ ይሆናል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውሳኔውን ዝርዝር ሁኔታ የሚያጠናውና ኤርትራ ለኢትዮጵያ መክፈል ያለባትን ቀሪ ክፍያ የምትፈፅምበትን ሁኔታ የሚከታተለው ይሆናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የካሣ ኮሚሽኑ አስቀድሞ እንደወሰነው በኤርትራ ወረራ ምክንያት ሁለቱ አገሮች አላስፈላጊ ወደሆነ ጦርነት ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጡ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዓ.ም.

ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር